ለውን ጥያቄ መሆን አለበት::

<u>አንደኛ</u>፣

መነሻ ነጥባችን ኢህአዴግ በማስናዳት ላይ ያለው ምርጫ ከዚህ ቀደም በአጼ ኃይለስላሴም ሆነ በደርግ አገዛዝ ስር ተካሄዱ እንደተባሉት ምርጫዎች፣ እስከጥቂት ዓመታት ድረስ በሌሎች አፍሪካ አገሮች ይካሄዱ እንደነበሩት ምርጫዎች ሥልጣን ላይ ያለውን ኃይል ለማጠናከር እንጂ ዴሞክራሲን ለማገዝ እንዳልሆነ መገንዘብና ይህንንም ግልጽ በሆነ ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝቦችም ሁሉ ዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ እንዲረዳው ማድረግ

<u>ሁለተኛ</u>፣

የነገሩን ዋናነት በመረዳት የኢህአዴግን የምርጫ ሂደት ፌዝ የሚያጋልጥ ብቻ ሳይሆን ነጻ ምርጫ ሲባል ምን እንደሆነ የሚያሳይና ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያን ህዝብ የሚቀሰቅስና የሚያታግል የተቀነባበረ የዲፕሎማሲ ዘመቻ የሚያካሂድ አንድ "ነጻ ምርጫ ለኢትዮጵያ" የሚል ራሱን የቻለ ኮሚቴ አቋቁሞ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ

<u>ሶስተኛ</u>፣

ይህንን ኮሚቴ በኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ ኃይሎች አማራጭ ምክር ቤት ዙሪያና ከሱ ውጭ ባሉ የሰላምና የዴሞክራሲ ኃይሎች ማቋቋምና ባስቸኳይ በዚህ ጥያቄ ላይ አንድ ሰፊ መግለጫና ይፋ ፕሮግራም አውጥቶ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ::

እነዚህን የትግል አግጣጫዎች ስንጠቁም ኢህአዴግ በወር ውስጥ ምርጫ ለማዘጋጀት ቀና ደፋ ማለቱን አጥተነው አይደለም:: ይህ መራራ ፌዝ ተካሄደም አልተካሄደም ገና ለረዥም ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝቦች የመራራ ትግል ዓላማ የሆነውን የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ጥያቄ አንገብጋቢነት አይቀይረውም:: የኢህአዴግ የምርጫ ፌዝ ከተካሄደ ይህ ምርጫ እንዴትና ለምን የተጭበረበረ እንደነበረ፣ በመሆኑም ውጤቱ ለምን የኢትዮጵያን ህዝቦች እንደማይመለከታቸው አጋልጦ ለነጻና ርእታዊ ምርጫ ገና ለረዥም ጊዜ ትግሉን የሚቀጥል ኮሚቴ ይሆናል:: ፌዙ ከተሳለፈ ደግሞ በሌላ ጊዜ ይደረጋል የሚባለው ምርጫ በርግጥም ነጻና ርእታዊ እንዲሆን መደረግ ስላለባቸው ነገሮችና መወሰድ ስላለባቸው ርምጃዎች ጥቆማዎችን እያደረገ የፖለቲካውንም የዲፕሎማሲውንም ትግል ያስተባብራል:: በየትም ሄዱን በየት የሰላማዊና የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እንደገና ወደአጥቂነት ደረጃ መሸጋገር ለዚህ አሰባሰብ ለሆነ የነጻና ርእታዊ ምርጫ ዓላማ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት የማይታለፍ የትግል ግዴታ ነው::